# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

27



ግንቦት ፩ — ፲፱፻፷፱ ዓ. ም.

## ርእሰ አንቀጽ

# መጭው ትግል የማይቀረው ድል

ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የአብዮቱን ችቦ ይዞ አሁን ከሚገኝበት ከፍተኛ የትግል ደረጃ የደረሰው የተጐናጸፋቸው ድሎች ሁሉ ለጠየቁት መስዋዕትነት ብቁ ሆኖ በመገኘቱ ነው ። የየካቲትን አብዮት ያፈነዳው ለብዙ ዘመናት የተጠራቀመው የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ የትግል ማዕበል ነው ። እዚያ ደረጃ ለመድረስ ብዙ ወገኖቻችን ታግለዋል ፤ ታሥረዋል ፤ ተገርፈዋል ፤ ተረሽነዋል ከዚያም ወዲህ ቢሆን ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በደሙና በመሥዋዕትነቱ ከቀንደኛ ጠላቶቹ እየተዋደቀ እንጂ በወርቅ ሣህን ላይ የቀረበለት የድል ገጸ በረከት የለም ።

በዚህ የነፃነት ትግልና ጉዞ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገው ነገር ግልጽ ነው ። በቀንደኛ ጠላቶቹ በፊውዳሊዝም ፤ በቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም መቃብር ላይ ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት ይታገላል ። በዚች ሀብታምና ለምለም ሀገሩ ታግሎ ተሰውቶና ድል አድርጐ ይቺን አገር ብሔረሰቦቹዋ በሙሉ በእኩልነት ያሸበረቁባት ፤ የአብዮታዊ ትግል ደሴት ብቻ ሳትሆን የብሔራዊ ነፃነትና ክብር ብርሃን ለመላ የአፍሪካ ጭቁኖች የሚፈነጥቅባት ፤ በትግሉና በመሥዋዕትነቱ ፍሬ ተገቢ ኩራት የሚሰማው ኩሩና ልበ ሙሉ ሕዝብ በነፃነትና በእኩልነት የሚኖርባት ፤ በዓለም ሕዝቦች ሸንጐ የታፈረችና የተደመጠች ሀገር ለመገንባት ይጣጣራል ።

ዛሬ የመጣ ትግልና ፈተና ቢመጣ የኢትዮጵያ ተራማጆችና ሰፊ ሕዝብ ይህንን ለዚች ዓይነቷ አብዮታዊት እናት ሀገር የሚያደርጉትን ታሪካዊ ተጋድሎ በምንም ዓይነት አያፈገፍጉበትም። የምናልመው ግብ ታላቅ እንደመሆኑ መጠን ከትግሉ የምንጠብቀውም ፈተናና መሥዋዕትነት የዚያኑ ያህል ታላቅ እንደሆነ እናውቃለን ። የምንጐናጸፈው ድል አኩሪ እንደመሆኑ መጠን ወደ ዚህ ድላችን በምናደርገው ጉዞ የሚገጥሙንን ችግሮች በሙሉ ልብና በቆራጥነት እንወጣቸዋለን። ጠላቶቻችን እጅግ ኃያል እንደመሆናቸው መጠን ትግሉ ረዥም መሆኑን እናውቃለን ። ግን ደግሞ የታሪክ ባለቤት የሆነውን ሰፊ ሕዝብ አንቅተን ፤ አደራጅተንና አስታጥቀን በሱ ተማምነን እስከ ታገልን ድረስ የመጨረሻው ድል የኛ እንደሚሆን ጨርሶ አንጠራጠርም ።

ዛሬ አብዮታችንና እናት አገራችን በብዙ ችግሮች ተወጥረው ተይዘዋል ። የአብዮታችንና የአንድነታችን ጠላቶች ተባብረው ከውጭ እየከበቡን ከውስጥ ደግሞ እየቦረቦሩን ናቸው ። በመጭው ጊዜ ይህ ከበባና ቡርቦራ እየተጠናከረና ሀገራችንን በይበልጥ ለማፈን እየሞከረ እንደሚሔድ በዚህም የተነሣ ትጥቃችንን ፈትን አብዮታችንን ለማስቀልበስና ሀገራችንን ብሔራዊ ሃፍረት ላይ በመጣል ካልተነሣን በስተቀር ብዙ ችግርና መሥዋዕትነት ለመቀበል ዝግጁ ሆነን መጠበቅ ይኖርብናል ።

ነገር ግን የመጣ ችግር ፤ የመጣ ውስብስብ ሁኔታ ቢመጣ አንድ ካሁኑ ሊረጋገጥ የሚችል ሐቅ አለ ። ዛሬ አብዮታዊት እናት አገራችንን ከየአቅጣጫው የያዟት ችግሮች በሙሉ ሊፈቱ የሚቻሉት በአብዮታችን መግፋትና ድል መምታት ብቻ ነው ። ምክንያቱም ባለፈው ርእሰ አንቀጻችን እንዳልነው የአብዮታችን ፤ የአንድነታችን ፤ የብሔራዊ ክብርና ነፃነታችን ጠንቅ የሆኑት ኃይሎች ያው ፊውዳሊዝም ኢምፔሪያሊዝም ፤ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምና እነሱ የሚያሽከረክሩአቸው አድኃሪ ኃይሎች ስለሆኑ ነው ።

ስለሆነም ጥያቄው የአብዮት ጥያቄ እንደመሆኑ መጠን መፍትሔውም ያለው ከሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ እጅ ውስጥ ነው ። ዛሬ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ የአብዮታችን የወደፊት ዕድልና የዚች እናት አገራችን ህልውና በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ እጅ ውስጥ ያለ ነገር ነው ። የትኛውም ችግር ቢሆን አብዮታዊ መፍትሔ ለማግኘት የሰፊውን ሕዝብ ተሳትፎ ይጠይቃል ።

የሰፊው ሕዝብ ተሳትፎ በምንልበት ጊዜ አብዮቱን በሚያራምድ መልክ የምንፈልገው ተሳትፎ የነቃ ፤ የተደራጀና የታጠቀ ሕዝብ ተሳትፎ ማለታችን እንደሆነ ግልጽ ነው ።

ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ ሀገራችንን ወጥረው የያዙትን ችግሮች ከአብዮቱ አንጻር በመፍታት የነቃ ተሳትፎ ያስፈልገዋል ። የነቃ ተሳትፎ ማለት ሀገራችንን ያጋጠሟትን ችግሮች ዕለት በዕለት የሚከታተል ፤ እነዚህ ችግሮች ከአብዮታችን ጋር ያላቸውን የማይነጠል ግንኙነት የሚረዳ ፤ በሀገሪቱ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚገኘውን የአብዮትና የፀረ—አብዮት ኃይሎች አሰላለፍ ፤ የነዚህንም ኃይሎች የኃይል ሚዛን በአጠቃላይ የተረዳ በዚህም በተያዘው ትግል ውስጥ ለማንና ለምን እንደሚዋጋ ጠንቅቆ ያወቀ ተሳትፎ ፤ ዞሮ ዞሮ ደግሞ የመጣው ትግል የመጣ መሥዋዕትነት ቢመጣ የመጨረሻው ድል የሱ እንደሆነ የማይጠራጠር ተሳትፎ ለማለት ነው ።

ይህ ተሳትፎ ኃይሉ በእጥፍ ድርብ እንዲጨምርና የአድኃሪዎችን የተደራጀ ኃይል ሰባብሮ ለመጣል እንዲችል የተደራጀ ተሳትፎ መሆን ይገባዋል ። ይኸንን ስንል ሁለት የተያያዙ የመደራጀት አቅጣጫዎች መጠቀም አለብን ። በአንድ በኩል የሰፊውን ሕዝብ የተደራጀ ተሳትፎለማስገኘትና ሰፊውን ሕዝብ በፈርጅ በፈርጁና በየደረጃው አደራጅቶ ለመምራት የሚቻል ግንባር ቀደምና ራሱም በይበልጥ የተደራጀ ኃይል ያስፈልጋል ። ይህንን ግንባር ቀደምና የተደራጀ አመራር ሊሰጡ የሚችሉ የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒንስቶች ኅብረታቸውን እያጠነከሩ መሔዳቸው የሰፊውን ሕዝብ ትግል ለመምራት ብቻ ሳይሆን በየፈርጁና በየደረጃው ለመደራጀት የሚያደርገውን ትግል በግንባር ቀደምትነት ለማስተባበር የሚረዳ መሣሪያ ነው ። ከዚሁ ጋር በጥብቅ ተያይዞ ግን ዛሬ በሀገሪቱ የሚገኙትን ፀረ ፊውዳል ፤ ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ቢሮክራቲክ ካፒታሊስት ኃይሎች በሙሉ በየፈርጃቸውና በየደረጃው አደራጅቶ ለአብዮቱ ማሰለፍ መቻል ያስፈልጋል ። ስለሆነም ዛሬ ከምንጊዜውም ይበልጥ ወዝ አደሩን ፤ አርሶ አደሩን ፤ መለዮ ለባሹን ፤ ጭቁን ሴት ፤ ወጣቶችን ፤ ሌሎች አገር ወዳድና ዲሞክራሲያዊ ኃይሎችን ለማደራጀት ሌት ተቀን መሥራትና መታገል ያስፈልጋል ።

በዚሁ አንጻር ደግሞ ይህ የነቃና የተደራጀ ሕዝብ አስተማማኝ የሆነ የአብዮቱ ኃይል እንዲሆን ከእግር እስከራስ የታጠቁ አድኃሪዎችን ለመቋቋምና ለመደምሰስ እሱም የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በሚፈቅደውና የዚች እናት ሀገሩ ህልውና በሚጠይቀው ልክ እንዲታጠቅ ያልተቆጠበ ጥረትና ተጋድሎ ማድረግ ያስፈልጋል ።

ባጭሩ ከመጭው የትግልና የተወሳሰበ ፈተና ወቅት አብዮታችንና እናት አገራችን በድል አድራጊነት እንዲወጡ ዛሬ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ የሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ተሳትፎ ለማሳደግ መታገል ያስፈልጋል ። ከየካቲት ወዲህ የተፈጠሩ ሕዝባዊ ድርጅቶች በንቃት ፤ በድርጅት በትጥቅ ከዕለት ዕለት እየዳበሩ እንዲሔዱ ፤ ድርጅቶች በሌሉበት ቦታ ደግሞ እንዲፈጠሩና እንዲያብቡ መታገል ያስፈልጋል ። በዚሁ አንጻር የማርክሲስት ሌኒንስቶችን ኅብረት ከዕለት ዕለት እያጠናከሩ መሔድና ወደ ውህደት ማሸጋገርና እየነቃ ፤ እየተደራጀና እየታጠቀ ለሚሔደው ሰፊ ሕዝብ አብዮታዊ የሆነ አመራር መስጠት ያስፈልጋል ።

በዚህ ትግል ውስጥ በተለይ ሰፊውን ሕዝብ ለማንቃትና በየፈርጁና በየደረጃው ለማደራጀት የሚደረገው ጥረት እንዲፋጠን አንቂና አደራጅ የሚሆኑ ካድሬዎችን አሁን ካለው እጥፍ ድርብ አድርጐ በሰፊው ሕዝብ ውስጥ ማሰማራት ያስፈልጋል ። የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ ቤትም አቋሙን ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ አጠናክሮ ከሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ተዋሕደው የሚያነቁትና የሚያደራጁት ካድሬዎች ለማበርከት ዝግጁና ብቁ ሆኖ መገኘት አለበት ።

አብዮታዊት ኢትዮጵያ ።